# ለክቡር አቶ ባይሳ ዋቅወያ —

## ስለቋንቋ መሠረተ ሐሳብ

ተፈራ ድንበሩ

March 16, 2018

ስለፊደል፣ ብሔራዊ ቋንቋ እና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕዝባችንን መብቶች እንዲሁም የመንግሥታት ተፅዕኖዎችንና ጭቆናዎችን በማስመልከት በየጊዜው በተከታታይ የጻፏቸውን አብዛኛዎቹን ጦማርዎችዎን አንብቤያቸዋለሁ። ለአገርዎ መልካም ከሚያስቡ ሰዎች መካከል አይዎታለሁ። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን ጠበብ እያደረጉ በመመልከት ሲጽፉ ዝም ከማለት ማስተካከያ ቢያደርጉ በማለት ይህችን  አጭር ጽሑፍ ፤ለርስዎ መጻፍና በኅብረተሰቡ መነበብ ግንዛቤን ያሰፋል ብዬ እገምታለሁ።

ይህ ጽሑፌ በተለይ በቅርብ ጊዜ ለፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ምላሽ በሚል የጻፉትን ይመለከታል። ፕሮፌሰሩ ራሳቸው መልስ ሊሰጡበት ከፈለጉ የራሳቸው ምርጫ ቢሆንም በኔ በኩል የተሰማኝን ለማካፋል ነው። የሥነጽሑፍዎ መንፈስ ቋንቋ በመንግሥት ድንጋጌ እንደሚቀረጽና እንደሚያድግ ያመለክታል። በመሠረቱ የመንግሥት ልሳን የሚሆን ቋንቋ መኖሩ፤ መንግሥት የሚጠቀምበት ብሔራዊ ቋንቋና ፊደል መኖሩ ሐቅ ነው፤ ሆኖም መንግሥትንና ቋንቋን ማገናኘት ከፈረሱ ጋሪው ይቀድማል ወይም ከጋሪው ፈረሱ ይቀድማል እንደሚባለው ዓይነት ክርክር ነው። ማንኛውም መንግሥት ብዙ ሕዝብ የሚጠቀምበትን ቋንቋ በብሔራዊነት ይጠቀምበታል እንጂ መንግሥት በአዋጅ የፈለገውን ቋንቋ ብሔራዊ ሊያደርገው ቢሞክር ፖሊቲካዊ ውሳኔ ሆኖ ለየሕዝብና ለአገር  የሚያስፈልገውን መሠረታዊ ነገር ይገታለል እንጂ ለአገርና ሕዝብ አይጠቅምም። በምሳሌ ለማስረዳት በበሬ ምትክ በጎችን አጥምዶ ለማረስ እንደመሞከር ነው። በጎችን ጠምዶ ማረስ ለምን አይቻልም ብለው ቢከራከሩ ይችላሉ። ነገር ግን በሬ እያለ በግ ጠምዶ ማረስ ይጥቅማል ወይ? የሚለው ምላሽ ይመስለኛል። አማርኛም እንዲሁ ነው፤ የመንግሥት ቋንቋ እንዲሆን ማንም አልመረጠውም፤ እርሱ ግን የብዙሐን አገልጋይ ስለሆነ የብዙዎቻችን የቅድመ አያት ቅድመ አያቶች የራሳቸውን አገር(አካባቢ) ቋንቋዎች ከዚህ ከአዲስ ንግግር ጋር አዋህደው ሲጠቀሙበት ቆይተው ወይም  ደረጃ በደረጃ የራሳቸውን አዲስ ቋንቋ ፈጥረው ሲያስተላልፉት  የልጅ–ልጅ–ልጅ–ልጆቻቸው ደግሞ  ከወላጆቻቸው ቅድመ–አያት–  ቅድመ  –  አያቶቻቸው  (የቀደሙ  ትውልዶች)  የወረሱትን  ከመቀበል  በስተቀር  ምርጫ እንዳልነበራቸው ሁሉ ቋንቋውም ቀስበቀስ አካባቢውን እየመሰለና ኅብረተሰቡም እያሻሻለውና እየቀረጸው መጥቶና ከትውልድ ወደትውልድ ተወርሶ ኅብረተሰቡ የራሱ አደርጎት አማርኛ የሚናገረውም ኅብረተሰብ አማራ ተባለ እንጂ እርስዎ እንዳሉት የፊውዳል ሥርዓቶች አማርኛን በማንም ላይ አልጫኑም። ላለመጫናቸው ትልቁ ምስክር አማርኛ በይፋ የመንግሥት ቁንቋ የሆነው ከ 11 ኛው እስከ 13 ኛው መቶ ክፍለዘመናት በቆየው በዛጉዌ ሥርወ–መንግሥት ሲሆን ዛጉዌዎች ደግሞ በብሔረሰብ ሳይገደቡ የሰፊውን ሕዝብ መግባቢያነት ተከትለው አማርኛን በመንግሥት ደረጃ ተቀበሉት እንጂ እስካሁን የራሳቸው ቋንቋ እንዳላቸው የታወቀ ነው።  አማርኛም ሆነ ሌላ ቋንቋ ዘር የማያውቅ፣ ፖሊቲካና ሥልጣን የማያውቅ አገልጋይ ስለሆነ አላጠፋም፤ አማርኛ ተናጋሪው ሕዝብም አላጠፋም፤ ይህ እንግዲህ

ሁሉንም ቋንቋ ተናጋሪ ይመለከታል፤ ለምሳሌ ኦሮሞ ያልነበሩ ወገኖች እንዲሁ ቀስበቀስ የራሳቸውን ትተው ኦሮምኛን የራሳቸው ሲያደርጉት ኦሮምኛ ብዙ ተናጋሪ ሊኖረው ችሏል፤ ተናጋሪዎቹም ኦሮሞ ተብለዋል። ኦሮሞ ቋንቋም አላጠፋም፤ ኦሮምኛ የተናገረው ኅብረተሰብም አላጠፋም፤ መለኮታዊ ሳይሆን የተፈጥሮ ሕግ ነው። እርስዎ ሂደት ያሉት ግን የቋንቋውን ነባራዊነት ወይም ተፈጥሯዊ አመጣጥ የሚሸፍን ግርድፍ ፖሊቲካዊ አገላለጽ እንጂ የእድገቱን ሁኔታ ግልፅ አያደርገውም።

ማንኛውም ቋንቋ እንደማንኛውም ተፈጥሯዊ ክስተት ይወለዳል፤ ያድጋል፤ ይሞታልም። አኳሁኑ ግን በዝግመታዊ ለውጥ እንጂ በአብዮታዊ ለውጥ አይደለም፤ ለዚህ ነው የተፈጥሮን አካሄድ የማይረዱ አብዮታውያን ወይም ወገንተኛ ፖሊቲከኞች የግንዛቤ ችግር የሚያጋጥማቸውና የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት መከተል የሚያዳግታቸው። የሚከተለውን አባባልዎን በደንብ ለሚያይ ሰው ሳይንሱና ፖሊቲካው ይደባለቅበታል፡-

…ህዝቦች በራሳቸው ቋንቋ የመጠቀም መብታቸው ተጠብቆላቸው በመከባበርና በእኩልነት እንዲኖሩ፣ ብሎም ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ያላንዳች ገደብ ለመዘዋወርና ለመስራት እንዲችሉ….የህዝቦች በነጻ የመንቀሳቀስ ክስተት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል፣ ቀስ እያለ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ እንዲከበርላቸው ሲጠይቁ የነበረው ክልላዊ መብታቸው ያለክልልም እንደሚከበርላቸው እያወቁ ሲመጡ፣ ራሳቸውን ከክልል ባሻገር ማየት ይጀምራሉ፣ በሂደትም አንዳንዶች ቋንቋዎች ተፈላጊነታቸው እየቀነሰ ብሎም እየከሰሙ ይሄዳሉ። ህዝቡም፣ ቋንቋን ከመብትና ከማንነት ጥያቄ አንጻር ማየት ይተውና ከግል ጥቅም ጋር ብቻ ማዛመድ ይጀምራል፥ ኢትዮጵያም “ብሄራዊ አገር” ወይም በእንግሊዝኛ nation-state ልትሆን የምትችለው ይህንን ተፈጥሮያዊ ሂደት ስትከተል ብቻ ነው።

በተጠቀሰው አንቀጽ ውስጥ ያሉት ሐረጎች ወርቃወርቅ ሆነው ተስፋን የሚገልጹ ሲሆን ከነሱ ውስጥ የተሠመረባቸው ሐረጎች ጋር የተያያዙ ሐሳቦች ግን የሚያመለክቱት ተፈጥሯዊ እድገትን ሳይሆን ንቃተኅሊናን (ፖሊቲካዊ ግንዛቤን) ነው። በክልል ከታጠሩ የፖሊቲካና የመንግሥት ተጽዕኖ ውስጥ መውደቅ እንጂ ዓለም አቀፋዊ የተፈጥሮ ሕግን የመከተል ነፃነት ሊኖራቸው አይችልም። ቋንቋ የሚፈጠረው በኅብረተሰብ ነፃ ግንኙነት ነው፤ የሚያድገውም በኅብረተሰቦች ነፃ ግንኙነቶች ማደግ ነው፤ የሚሞተውም ኅብረተሰቦችን ማገናኘት ሲያቅተው ነው። እዚህ ላይ መታየት የሚችለው የሥነጽሑፍ መስፋፋት ለቁንቋ እድገት የሚኖረው ሚና ነው፤ አንድን ቋንቋ በቃልም ሆነ በሥነጽሑፍ የሚጠቀሙበት ኅብረተሰቦች ብዛት መጠን የቋንቋውን የእድገት ደረጃም ሆነ አለማደግ ሊወስን ይችላል። ማንኛውም ቋንቋ የአንድን ማኅበረሰብ ድንበር አልፎ ወደሌሎች ኅብረተሰቦች በሄደ መጠን ለእድገት ያለው ዕድል ከፍተኛ ይሆናል፤ ቋንቋው ድንበርን አልፎ እንዲሄድ የሚያደረገው ደግሞ ነፃ የኅብረተሰብ መደባለቅ እንጂ በማህበራዊ ክልል መወሰን አይደለም። ፕሮፌሰር ጌታቸው እንግዲህ መንግሥት በሕዝብ ቋንቋ ተጠቃሚ እንጂ ወሳኝ መሆን አይችልም፤ ቋንቋም እንዲያድግ ክልል የሚባለው የአፓርታይድ ክፍፍል ፈርሶ የአንድ አገር አስተዳደራዊ ክፍፍል መልከአምድራዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባለው መንገድ መዋቀር አለበት ማለታቸው ፖሊቲካዊ ሳይሆን ሳይንሳዊ ሐቅ ነው። ነፃ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ባለበት ሁኔታ ሕዝቦች ማንም ሳያስገድዳቸው ወይም በራሳቸው ፈቃድ የዳበረ ባህል ካለው ኅብረተሰብ ጋር መገናኘትን ይፈልጋሉ። በቴክኖሎጂ ያደገን አገር ባህል ከነቋንቋው ወስደውት የራሳቸውም ሊያደርጉት ይችላሉ ። ለምሳሌ በሁሉ መልካም የሆነች ልጃገረድ ብዙዎች ሊያጪት እንደሚሹ ቋንቋም ከሚገልጸው ባህል ተወዳጅነት የተነሣ በብዙዎች ተፈልጎ ሊተላለፍ ይችላል። ለምሳሌ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዝን፣ ቴሌፎን፣ቢስክሌት፣ ሳሎን፣ ብሩሽ፣…ወዘተ በቴክኖሎጂ ውጤት ጠቃሚነታቸው የተነሣ በተፈጥሮ ሕግ መሠረት ቃላቱም የዓለም ቋንቋዎች መሆን ችለው በብዙ ኅብረተሰቦች ባህል ውስጥ ገብተዋል። እኛም እንዲሁ ባንዲራ፣ መኪና፣ ገራዥ፣ ስኒ፣ ኩባያ፣ በረንዳ፣ ሱቅ፣ ጣሳ፣ ቀሚስ፣ ሳምቡሳ … ወዘተ የተባሉ ቃላትን ከሌሎች ወስደን የራሳችን አድርገናቸዋል። የባዕድ ወይም የጠላት ናቸውና አንፈልጋቸውም

ሳንል በባህላችን ውስጥ ተቀበለናቸው ተጠቀምንባቸው፤ ወደፊትም ዛሬ ዳብረውና አድገው ያሉትን ባህሎች አልፈን ከነሱ የላቀ የቴክኖሎጂ ውጤት ኖሮን ወይም ተፎካካሪያቸው ካልሆን በስተቀር እንደዚህ ያሉ ቃላትን መጠቀማችን አይቀርም። ተወዳዳሪ መሆን ካልቻልን ደግሞ የሁላችንም ቋንቋዎች በዓለም ቋንቋዎች የመዋጥ/የመሞት/ ዕድል አላቸው። በተመሣሣይ ሁኔታ ጉዲፈቻ፣ ማረሻ፣ እርካብ፣ መጣብር፣ ማሲንቆ፣ ጎራዴ፣ ሞፈር፣ ገበሬ፤ ዝናር... ወዘተ በነበረን የቴክኖሎጂ ደረጃ እርስበርሳችን የተዋዋስናቸው ቃላት ናቸው። የባህል እድገት ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር ስለሚሄድና ቲክኖሎጂ ደግሞ አቅምን ከማሳደግና በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ከመሆን ጋር የተያያዘ ስለሆነ የተጠናከረ ባህል እንዲኖረን አቅምን ማሳደግ የምንችለው በኅብረት እንጂ በተናጥል አይደለም፤ በተናጥል ስንሄድ ግን እንኳን ሞፈርና ቀንበርን ወደአዲስ ቲክኖሎጂ ልንለውጥ ቀርቶ የሌሎችን ቲክኖሎጂም መሸመት አቅቶን ጥገኞች ሆነን እንቀራለን። ከቋንቋ ባሻገር ያሉትንም ታላላቅ የአገር ጉዳዮች ማየት ያስፈልጋል። ስለሆነም አንድ ቋንቋ በመጀመሪያ በራሱ ቤተሰብ ውስጥ በነፃነት መስፋፋትና ማደግ አለበት፤ ይህ ደግሞ በፖሊቲካዊ ውሳኔ የላቲንን ፊደል በመጠቀም ሳይሆን በራሳችን የግዕዝ ፊደል ስንጠቀም ነው። በአንድ ፊደል መጠቀም አንዱ የሌላውን ሁሉ ለመማር ይቀለዋል የበለጠ ያቀራርበዋል፤ በመስተጋብሩ ሒደት የሚያይለው ይወጣል፤ ያየለው የሁላችንም ይሆናል።

ብዙ ጊዜ የምንሰማው በኦሮሞ ምሁራን ጥናታዊ አስተያየት መሠረት ነው ላቲን ለኦሮምኛ መጠቀሚያ የሆነው ይባላል። ሆኖም በኦህዴድ ካድሬዎች በአንዳንድ ቀበሌዎች ሕዝቡ ቁቤን ስለመቀበሉ ድጋፍ እንዲሰጥ ከተደረገው ፖሊቲካዊ አሠራር በስተቀር በግዕዝ ፊደል ይጠቀም ነበረው የኦሮሞ ሕዝብ ላይ የተደረገ ትክክለኛ ጥናት ካለመኖሩም በላይ በቁቤ ተምረው የተመረቁ ወጣቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ ያጋጠማቸውን ችግር ያጠና ስለመሆኑ አይታወቅም። እዚህ ላይ ለአንባቢ ግንዛቤ ይህችን ብጨምር፤ በናዝሬት አካባቢ በ 1980 ዎቹ ዓመታት ውስጥ አንድ አዛውንት ልጅዎ በኦሮምኛ ነው ወይስ በአማርኛ ቢማር የሚመርጡት ተብለው ይጠየቃሉ። መልሳቸው “ኦሮምኛ የራሳችን ስለሆነ ከየቤታችን ጀምሮ እንዳንነጋገር የከለከለን ነገር የለም፤ የኔ ልጅ በአማርኛ ቋንቋ ተምሮ ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር ቢግባባ እመርጣለሁ” ብለው መለሱ። ምርጫቸውን ብቻ ሳይሆን ምክንያታቸውን ይመለከቷል።

በክልል በታጠረ ኅብረተሰብ ወይም ነፃ የሕዝብ እንቅስቃሴ በሌለበት ሁኔታ ቋንቋ ማደግ ወይም መዳበር አይችልም። ነፃ ማለት በተሽከርካሪ ወይም በአጋሰስ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የመጓጓዝ መብትን ብቻ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ መሆን አለበት፤ ይኸውም ማንኛውም ሰው በፈለገው ክፍለሀገር ኑሮውን መሥርቶ ምንም ዓይነት የመገለል መንፈስ ሳይኖርበት ያለሥጋት በማንኛውም የሙያ ወይም የሥራ መስክ በንግድ፣ ወይም በማናቸውም ኢንደስትሪ ሠርቶ ንብረት አፍርቶ ገብይቶና ተገበያይቶ መኖርን ይመለከታል። ክልሎች በታሪፍና በተለያዩ ሕጎች የቋንቋ አጠቃቀምን ጨምሮ በታጠሩበት ሁኔታ ግን ከሌላ አካባቢ መምጣቱን እና ራሱን ለይቶ እንዲያይ ተደርጎ በማንነቱ ላይ ተፅዕኖ ስለሚፈጥርበት ደህንነት ስለማይሰማው ነፃነቱ የተገታ ነው። ይህም የኅብረተሰቦችንን ተደባልቆ መኖር የሚገታ ስለሆነ በማኅበራዊ አኗኗርና በባህል መገደብ የተነሣ በቋንቋም እድገት ላይ ተጽእኖ ያደርስበታል።

“አንዳንድ ቋንቋዎችን ሳይማሩ ቢቀር አይጎዳም” የሚለው አባባል በፖሊቲከኛ ሰው ሲታይና በቋንቋ ምሁር ሲታይ ልዩነት ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ እየሞተ ያለን ቋንቋ በትምህርትቤት ተማሪዎች እንዲማሩት ከማድረግ ብዙ ሕዝብ የሚናገረውን ቋንቋ እንዲማሩት ማድረጉ የተሻለ ነው። ግዕዝን ወይም አርጎብኛን በትምህርትቤት ተማሪዎች እንዲማሩት ከማድረግ አማርኛንና ኦሮምኛን እንዲማሩት ማድረግ ሊጠቅም ይችላል፤ ምክንያቱም ብዙ ሕዝብ የሚገለገልባቸው ቋንቋዎች ናቸው። ከዚህ ጋር አብረው በጥንቃቄ እንዲያዩ የሚያስፈልገው “ቋንቋዎች ሁሉ እኩል ናቸው” የሚለውን አገላለጽ ነው፤ ቋንቋ ለሚጠምበት ማኅረሰብ በቂ ነው፤ የቋንቋው ባለቤት በዚያ በቋንቋው በደንብ ያለችግር መግባባት ይችላል ማለት ነው። እኩልነቱ የሚታየው ኅብረተሰቡንና ባህሉን ከራሱ ቋንቋ ጋር ብቻ

መሆኑን ልብ ይሏል። ይህ ማለት ባህላቸውና የእድገቱም መጠን አንድ ደረጃ ላይ ነው ማለት ሲሆን፤ በሥነጽሑፍና በቴክኖሎጂ ባህል በበለጸገ ቋንቋ የሚጠቀም ሌላ ኅብረተሰብ ደግሞ ቋንቋው ከራሱ አልፎ ሌሎችም ኅብረተሰቦች የሚጠቀሙበት እየሆነ እያለ ከሌላ እንደዚህ ካላደገ ቁንቋ ጋር እኩል ነው ብሎ መከራከር አይቻልም። እኩል ሊሆን ያልቻለ ቋንቋ ደግሞ በዝግምታ እየተዳከመ መሔዱ ተፈጥሯዊ ሂደት ነው፤ ከዚህ አንፃር ነው እንግዲህ አንዳንድ ቋንቋዎች እስከሞት የሚደርሱት። ለምሳሌ ቋንቋዎች እኩል ናቸውና እኩል መብት አላቸው ተብሎ ከ 80 የሚበልጡት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ብሔራዊ ቋንቋ ይሁኑ ማለት ነው፤ ይህ ግን በማናቸውም መስፈርት አይቻልም፤ እርስዎ ቃል በቃል አላሉትም እንጂ የጽሑፍዎ እንድምታ ግን ያንን ያስከትላል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በላቲን ፊደል በመጠቀሙ የኦሮሞ ሕዝብ ተደስቷል ማለትዎ የፖሊቲካ ይዘት እንጂ በእውነት ላይ ያልተመረኮዘ ነው። ፈረንሳዮች፣ እንግሊዞች፣ ጀርመኖችና ሌሎች አውሮፓውያን በአንድ ፊደል በመጠቀማቸው በቋንቋና በባህል መወራረሳቸውንና በቴክኖሎጂም ለማደግ ምን ያህል እንደጠቀማቸው ታይቷል፡፡ የግዕዝ ፊደልም ለአማርኛ ብቻ ሳይሆን ለኦሮሞኛና ለሌሎችም ቋንቋዎች ያለችግር አገልግሎት ሰጥቷል፤ ኢትዮጵያውያን ቢጠቀሙበት የበለጠ ይግባቡበታል፤ አንዱ የሌላውን ቋንቋም ለማወቅ እጅግ ይረዳል፤ "አማርኛ ተናጋሪዎችን ለማስደሰት ሲባል..." ብለው የገለጹት አገላለጽ ግን ግልባጩ ሲታይ የማያውቁት አገር ይናፍቃል እንደተባለው ከአማርኛ ተናጋሪዎች ይልቅ ሮማውያንን ለማስደሰት ያደሉ ይመስላል። አማርኛ ተናጋሪዎች ወይስ ሮማኖች የሚቀርቡዎት? ከተጨባጭ ጥቅሞቹ በተጨማሪ ግዕዝ የራሳችን በመሆኑም ያኮራናል፤ አይሻለንም ለማለት ምክንያት የሚፈልጉ ከሆነ ግን ክርክርዎ በነበራዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ጠበብ ባለ ፖሊቲካዊ አመለካከት ላይ የተመሠረተ አቋም ስለሆነ ኢትዮጵያዊነትን ብቻ ሳይሆን አፍሪቃዊነትዎን ጭምር ከሚክዱት ውስጥ ሊያስደምርዎት ነው። ምክንያቱም በትክክለኛ የታሪክ ግንዛቤ ላይ ባልተመረኮዘና በነተስፋየ ገብረአብ በተጻፈ ድርሰት የተገነባውን የአኖሌ የጥላቻ ሐውልት እያየ በፈጠረው ንቃተኅሊና የፖሊቲካ መስመር የያዘውን ወገናችንን አስተሳሰብ ይመስላል። ባአማርኛና ኦሮምኛ ቋንቋዎች ላይ የሙያ ጥናት ተደርጎ ከ 37 ዋናዋና የግዕዝ ፊደሎች መካከል አንዱን ብቻ አሻሽሎ ለኦሮምኛ መጠቀሚያነት እንዲውል ማድረግ የሚያስገኘውን የመዋዕለ–ንዋይና የጊዜ ጠቀሜታ እንዳልተቀበሉት ያሳያል። አማርኛና ትግርኛ የሳባን ፊደል ሽሙቱ የሚለውን አገላለጽዎን ማ እንደሚቀድምና ማ እንደሚከተል በጥናታዊ መረጃ እንዲያሳዩን ለባለሙያዎቹ ቢተውላቸው ይሻል ይመስለኛል።

ለማጠቃለል ለቋንቋ እድገት መሠረቱ ፖሊቲካዊ ወይም መንግሥታዊ ድንጋጌ ሳይሆን ባህልን ማሳደግ ነው፤ ባህል ደግሞ የሚያድገው ኅብረተሰቦች ተገደው በሚፈጽሙት የዚህ ብሔረሰብ፤ የዚህ ክልል፤ የዚያ ክልል በሚል ማህበራዊ ማዕቀብ ሳይሆን የኅብረተሰቡ ባህል በሌሎች ተፈላጊ ሆኖ ድንበር ተሻግሮ እንዲሄድ ወይም እንዲመጣላቸው ሲፈልጉት ነው። ይህ የሚመጣው ደግሞ በሕዝቦች ነፃ ማኅበራዊ መስተጋብር፣ በነፃነት በመኖርና በመንቀሳቀስ በነፃነት በመሥራት፣ በነፃነት ባህልንና ቴክኖሎጂን ያለገደብ በማሳደግ ነው። የባህልና ቴክኖሎጂ እድገት የማንኛውም ሕዝብ እድገት ድንበር ማለፍ ሲችል ያኔ ቋንቋም ያድጋል። ስለሆነም ክቡር አቶ ባይሳ ማንኛውም ቋንቋ ተጽዕኖ ሳይደረግበት ወይም ልዩ ሞግዚት ሳያስፈልገው በነፃ ገበያ ተወዳድሮ የማደግ ወይም ያለማደግ ዕድሉ እንደተጠበቀ ሆኖ እኛ ዛሬ ስለቋንቋ እድገት ከመጨነቃችን በፊት መታገል ያለብን ኅብረተሰቡ ከማናቸውም ክፋፉይ ጎጠኛ ሥርዓት ነፃ ሆኖ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ ሠርቶ አገር መገንባት እንዲችል እና ቴክኖሎጂን ማሳደግ እንዲችል የሚያደርገው ከራሱ የተገኘ የራሱ መንግሥት እንዲኖረው ማድረግ ነው።

ተፈራ ድንበሩ